http://ethcriminalawnetwork.com

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በፍትህ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር ፍ/ጠ/ፌ/ዐ/ዐ/4521
Re.NO
ቀን 14-02-08
Date

ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

ልደታ ምድብ 19ኛ ወንጀል ችሎት

<u>አዲስ አበባ</u>

የፌ/ዐ/ሕግ/መ/ቁ.452/0

የፌ/ፖ/ወ/ም/መ/ቁ.232/08

የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት ወ/መ/ቁ

ከሳሽ-------------የፌደራል ዐ/ህግ

ተከሳሾች-----------1ኛ. ጉርሜሣ አያና ወየሳ

የትውልድ ዘመን፡- 1976

እድሜ

የትዳርሁኔታ ፡-ያገባ

ስራ

አድራሻ፡- ኦሮሚያ ክልል ኦሮሚያ ልዩ ዞን ብራዩ ከተማ

3-09-08

2ኛ. ደጀኔ ጣፋ ገለታ

የትውልድ ዘመን ፡- 1964

እድሜ

የትዳር ሁኔታ ፡- ያገባ

ስራ፡- የህግ ባለሙያ

አድራሻ፡- ኦሮሚያ ክልል ቡራዩ ወረዳ ቡራዩ ከተማ የቤ/ቁ.82

3ኛ. አዲሱ ቡላላ አባወልታ

የትውልድ ዘመን ፡-1981

እድሜ

የትዳር ሁኔታ፡- ያላገባ

ስራ፡- የፋይናንስ አስተዳደር

አድራሻ፡- አ/አበባ ከተማ ን/ስ/ላ/ክ/ከ ፲፯ ወረዳ 10 የቤ/ቁ---

ቴሌ ፋክስ 755061
Fex ---------------
ስልክ 764014
Tel. 51 50 99
የመ.ሣ.ቁ. 1370
P.O. Box 1370
አዲስ አበባ
Addis Ababa
ኢትዮጵያ
Ethiopia
"ፍትህ በተለወጠ አመራር ፣ በተለወጠ ሠራተኛ ፣ በተለወጠ ተቋም፡"

http://ethcriminalawnetwork.com



4ኛ. በቀለ ገርባ ዳኮ

የትውልድ ዘመን፡- 1953

እድሜ

የትዳርሁኔታ ፡-ያገባ

ስራ መምህር

አድራሻ፡- ኦሮሚያ ክልል አዳማ ከተማ

5ኛ. አብደታ ነጋሳ ፊዪ

የትውልድ ዘመን፡-1984

እድሜ

የትዳር ሁኔታ ፡- ያገባ

ስራ፡- አየር መንገድ ቴክኒሽያን

አድራሻ፡- አዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የቤ/ቁ/----

6ኛ. ገላና ነገራ ጅማ

የትውልድ ዘመን፡-1980

እድሜ

የትዳርሁኔታ፡- ያገባ

ስራ፡- የለውም

አድራሻ፡- ኦሬሚያ ክልል ኦሮሚያ ልዩ ዞን ቡራዩ ከተማ

7ኛ. ጭምሳ አብዲሳ ጃፈሮ (ቅጽል ስም ደጀኔ አብዲሳ)

የትውልድ ዘመን ፡- 1983

እድሜ

የትዳርሁኔታ ፡- ያላገባ

ስራ፡- የለውም

አድራሻ፡- ኦሮሚያ ክልል ፊንፊኔ ዙሪያ ዞን ቡራዩ ወረዳ

ቡራዩ ከተማ



unverified

http://ethcriminalawnetwork.com

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በፍትህ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር.........................
Re.NO
ቀን.................................
Date

8ኛ. ጌቱ ግርማ ቶሎሳ

የትውልድ ዘመን ፡- 1998

እድሜ

የትዳርሁኔታ ፡- ያላገባ

ስራ፡-

አድራሻ፡- ኦሮሚይ ክልል ኦሮሚያ ልዩ ዞን ሱሉልታ ወረዳ
ሱሉልታ ከተማ ቀበሌ 01

9ኛ. ፍራኦል ቶላ ዳዲ

የትውልድ ዘመን ፡- 1982

እድሜ

የትዳርሁኔታ ፡- ያላገባ

ስራ፡-

አድራሻ፡- ኦሮሚይ ክልል ጅማ ዞን ጅማ ከተማ

10ኛ. ጌታቸው ደረጀ ቱጁባ

የትውልድ ዘመን ፡- 1985

እድሜ

የትዳርሁኔታ ፡- ያላገባ

ስራ፡-

አድራሻ፡- ኦሮሚያ ክልል ም/ሸዋ ዞን ኤጀሬ ወረዳ

11ኛ. በየነ ሩዳ ጅዱ

የትውልድ ዘመን ፡- 1963

እድሜ

የትዳርሁኔታ ፡-

ስራ፡- መምህር

አድራሻ፡- ኦሮሚያ ክልል ም/ሸዋ ዞን አምቦ ከተማ
ቀበሌ04

ቴሌ ፋክስ 755061 ስልክ 764014 የመ.ሣ.ቁ. 1370 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Fex ---------------- Tel. 51 50 99 P.O. Box 1370 Addis Ababa Ethiopia

"ፍትህ በተለወጠ አመራር ፣ በተለወጠ ሠራተኛ ፣ በተለወጠ ተቋም"



unverified

http://ethcriminalawnetwork.com

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በፍትህ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር........................
Re.NO
ቀን................................
Date

12ኛ. ተስፋዬ ሊበን ቶሎሳ

የትውልድ ዘመን :- 1968

እድሜ

የትዳርሁኔታ :-

ስራ:- መምህር

አድራሻ:- ኦሮሚያ ክልል ደ/ም/ሸዋ ዞን ወሊሶ ከተማ

ቀበሌ04--

13ኛ. አሸብር ደሳለኝ በሪ

የትውልድ ዘመን :- 1977

እድሜ

የትዳርሁኔታ :-

ስራ:-

አድራሻ:- ኦሮሚያ ክልል ም/ሸዋ ዞን አምቦ ወረዳ ቀበል 01

14ኛ. ደረጀ መርጋ ደበሎ

የትውልድ ዘመን :- 1981

እድሜ

የትዳርሁኔታ :-ያላገባ

ስራ:- መምህር

አድራሻ:- አ/አበባ ከተማ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 02 የቤ/ቁ/-----

15ኛ.የሱፍ አለማየሁ ሂሬጋ

የትውልድ ዘመን :-1988

እድሜ

የትዳርሁኔታ :- ያላገባ

ስራ

አድራሻ:- ኦሬሚይ ክልል ቄለም ወለጋ ዞን ዓዳማ ወረዳ ዓዳማ ከተማ

ቀበሌ 02



unverified

http://ethcriminalawnetwork.com



16ኛ. ሂካ ተክሉ ኩቱ

የትውልድ ዘመን ፡- 1986

እድሜ

የትዳርሁኔታ ፡- ያላገባ

ስራ

አድራሻ፡- ኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ ዞን ዓዳማ ወረዳ ዓዳማ ከተማ

17ኛ. ገመቹ ሻንቆ ግዲ ቅፅል ስም ዴክማ

የትውልድ ዘመን ፡- 1982

እድሜ

የትዳርሁኔታ፡-ያገባ

ስራ፡- አስተማሪ

አድራሻ፡- ኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ ዞን የመልጊ ወለል ወረዳ ተጂ ከተማ

18ኛ. መገርሳ አስፋው ፊይሳ

የትውልድ ዘመን፡- 1984

እድሜ

የትዳርሁኔታ፡- ያላገባ

ስራ፡-አየር መንገድ ቴክኒሺያን

አድራሻ፡- አ/አበባ ከተማ አራዳ ክ/ከ/ ወረዳ --የቤ/ቁ/---

19ኛ. ለሚ ኤደቶ ገረመው

የትውልድ ዘመን ፡- 1988

እድሜ

የትዳርሁኔታ፡- ያላገባ

ስራ

አድራሻ፡- ኦሮሚያ ክልል ቡራዩ ከተማ ለኩከታ ቀበሌ



unverified

http://ethcriminalawnetwork.com



20ኛ. አብዲ ታምራት ዴሲሳ

የትውልድ ዘመን ፡- 1982

እድሜ

የትዳርሁኔታ ፡- ያላገባ

ስራ፡- የግል ሥራ

አድራሻ፡- ኦሮሚያ ክልል ኦሮሚያ ልዩ ዞን ቡራዩ ወረዳ

ቡራዩ ከተማ የቤ/ቁ.---

21ኛ. አብዲሳ ኩመሳ ገኤሳ

የትውልድ ዘመን 1983

እድሜ

የትዳርሁኔታ ፡- ያ ላገባ

ስራ

አድራሻ፡- አዲስ አበባ ከተማ ን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 11የቤ/ቁ/--

22ኛ. ሀልከኖ ቆንጮራ ጉሮ

የትውልድ ዘመን ፡- 1984

እድሜ

የትዳርሁኔታ ፡- ያገባ

ስራ፡- የለውም

አድራሻ፡- ኬንያ አገር ሞያሌ ከተማ ቀሌ ሴሲ የቤ/ቁ.----

**1ኛክስ**

**ከ1ኛ እስከ 13ኛተከሣሾች ላይ ብቻ**

**ወንጀሉ**

በ1996 ዓ/ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 35፣38፣ 32/1/ሀ/ እና የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 3 ንኡስ አንቀጽ 1፣3፣4 እና 6 ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ፡፡



unverified

http://ethcriminalawnetwork.com

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በፍትህ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር.......................
Re.NO
ቀን..............................
Date

## የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሣሾች ቀኑና ወሩ በውል ተለይቶ ባልታወቀ ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ከሌሎች ለጊዜው ስማቸው ካልታወቁ ግብረ አበሮቻቸው ጋር በመሆን የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንገረስ (ኦ.ፌ.ኮ) የፖለቲካ ድርጅት አባልና አመራር በመሆን ይህንን የፖለቲካ ድርጅት እንደሽፍን በመጠቀም እራሱን የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦ.ነ.ግ) ብሎ የሚጠራው በሰው ህይወት ፣ አካል ላይ እና በንብረት ላይ ጉዳት በማድረስ የፖለቲካ ስልጣን በሀይል ለመያዝ የሚንቀሳቀሰው እና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሽብር ድርጅት ተብሎ የተሰየመው የሽብር ድርጅት ውስጥ አባል በመሆን የሽብር ድርጅቱን አላማ ለማሳካት በሀገሪቱ ውስጥ ሁከትና ብጥብጥ እንዲነሣና በሰው ሕይወት ፣ ደህንነት እና ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዲደርስ በማድረግ በመንግስት ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ሕገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በሀይል በመናድ የመንግስትን ስልጣን ለመያዝ በማሰብ የአዲስ አበባና በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን የጋራ ማስተር ኘላን እና የኦሮሚያ ከተሞች የእድገት ኘላን የኦሮሚያን ህዝብ ቋንቋ ና ባህል የሚያጠፋ የኦሮሞን ህዝብ ከመሬቱ የሚያፈናቅል ነው በማለት እንደፓርቲ ወስነው የስራ ክፍፍል በማድረግ በተለያዩ የኦሮሚያ ከተሞችና ቀበሌዎች ላይ ህብረተሰቡ ወደ አመፅ እንዲገባ በማድረግ ሲቀሳቀሱ የነበረና በዚህም ምክንያት መሰረተ ልማት እንዲቋረጥ፣በመንገዶች ላይ ጉዳት እንዲደርስ እና በርካታ ሰው እንዲሞት ፣ 122 ሰው በላይ ከባድና ቀላል የአካል ጉዳት እንዲደርስ እና በአጠቃላይ ከ122,394,391.75/ አንድ መቶ ሃያ ሁለት ሚልዮን ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሶስት መቶ ዘጠና አንደ በር ከሰባ አምስት ሳንቲም/ በላይ በተለይም በመንግስት ፣ በግለሰብ ፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ንብረት ላይ ውድመትና ጉዳት እንዲደርስ ያደረጉ በመሆኑ በተለይም

### 1ኛ ተከሳሽ ጉርሜሣ አያኖ

ተከሳሹ ቀኑ ባልታወቀ ከጥቅምት ወር 2008 ዓ/ም ጀምሮ በኦሮሚያ ክልል ቡራዩ ከተማ ላይ የአዲስ አበባና የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን የጋራ ማስተር ኘላን እና የኦሮሚያ ከተሞች የእድገት ኘላን የኦሮሚያን ህዝብ ቋንቋ ፣ ባህል የሚያጠፋና የኦሮሚያን ህዝብ ከመሬቱ የሚያፈናቅል በመሆኑ ማስተር ፕላኑ እና የኦሮሚያ ከተሞች እድገት ኘላን ከመፅደቁ በፊት በተለያዩ የኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኙ

ቴሌ ፋክስ 755061 ስልክ 764014 የመ.ሣ.ቁ. 1370 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Fex ---------------- Tel. 51 50 99 P.O. Box 1370 Addis Ababa Ethiopia
"ፍትህ በተለወጠ አመራር ፣ በተለወጠ ሠራተኛ ፣ በተለወጠ ተቋም፣"



unverified

http://ethcriminalawnetwork.com



ወጣቶችን በማነሳሳት በሰው ህይወትና ንብረት ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማድረግ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ከተሞችና ቀበሌዎች ውስጥ ማንኛውንም የህዝብ አገልገሎቶች እንዲቋረጥ በማድረግ በመንግስት ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ማስተር ፕላኑና የኦሮሚያ ከተሞች እድገት ኘላን እንዳይፀድቅ ማድረግ ፣ የኦሮሚያን ህዝብ ነፃ ለማውጣት የኦሮሞ ህዝብ አመፁን ከዳር እስከዳር እንዲያነሳ በማድረግ መንግስትን ከስልጣኑ ማውረድ  አለብን በማለት ቅስቀሳና የማነሳሳት ተግባር በመፈፀም እና መቀመጫውን ውጭ ሀገር ላደረገው  የኦ.ነ.ግ ልሳን ለሆነው የኦሮሞ ሚዲያ ኔቶርክ ( O. M. N ) ከላይ በተገለፀው አግባብ መረጃዎችን በመስጠትና አመፁ በአንድ ጊዜ በሁሉም የኦሮሚያ ከተሞች መነሳት አለበት በሚል ቅስቀሳ በማድረጉ በተለያዩ አካባቢዎች ላይ እረብሻና አመፅ እንዲነሳ ያደረገ በመሆኑ

<u>2ኛ ተከሳሽ ደጀኔ ጣፋ</u>

ቀኑ ባልታወቀ ከጥቅምት ወር 2008 ዓ/ም ጀምሮ በኦሮሚያ ክልል ቡራዩ ከተማ ላይ የአዲስ አበባና የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን የጋራ ማስተር ኘላን እና የኦሮሚያ ከተሞች የእድገት ኘላን የኦሮሚያን ህዝብ ቋንቋ ፣ ባህል የሚያጠፋና የኦሮሚያን ህዝብ ከመሬቱ የሚያፈናቅል በመሆኑ ማስተር ፕላኑ እና የኦሮሚያ ከተሞች እድገት ኘላን ከመፅደቁ በፊት በተለያዩ ኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶችን በማነሳሳት በሰው ህይወትና ንብረት ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማድረግ ፣ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ከተሞችና ቀበሌዎች ውስጥ ተማሪዎች ትምህርት ቤት ገብተው እንዳይማሩ ፣ አስተማሪዎች እንዳያስተምሩ ፣ የትራንስፖርት እንቅስቃሴ እንዳይኖር ማድረግ ፣ ግብር ለመንግስት እንዳይከፈል በማድረግ በመንግስት ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ማስተር ፕላኑና የኦሮሚያ ከተሞች እድገት ኘላን እንዳይፀድቅ ማድረግ  አለብን በማለት ቅስቀሳና የማነሳሳት ተግባር በመፈፀም እና መቀመጫውን ውጭ ሀገር ላደረገው  የኦ.ነ.ግ ልሳን ለሆነው የኦሮሞ ሚዲያ ኔቶርክ ( O. M. N ) ከላይ በተገለፀው አግባብ መረጃዎችን በመስጠትና አመፁ በአንድ ጊዜ በሁሉም የኦሮሚያ ከተሞች መነሳት አለበት በሚል ቅስቀሳ በማድረጉ በተለያዩ አካባቢዎች ላይ እረብሻና አመፅ እንዲነሳ ያደረገ በመሆኑ



unverified

http://ethcriminalawnetwork.com



3ኛ ተከሳሽ አዲሱ ቡላላ

- ቀኑ እና ወሩ በውል ተለይቶ ባልታወቀ 2006 ዓ.ም ኦሮሚያ ሚዲያ ኔትወርክ( O. M. N )- ኃላፊ እና ኦነግ አመራር ከሆነው ጃዋር መሀመድ ጋር በተደጋጋሚ ጊዜ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች በመገናኘት እና ገንዘብ እንዲላክለት በማድረግ በ2006 ዓ.ም በአዲስ አበባ እና አዲስ አበባ ዙሪያ የተቀናጀ ማስተር ፕላን እንደ ሽፋን በመጠቀም በክልሉ የተቀሰቀሰውን የሽብር አመፅ ያስተባበሩ እና የመሩ የሽብር ቡድኑን አባሎች በህግ እንዳይጠየቁ ለማድረግ ሲንቀሳቀስ የነበረ በመሆኑ፣
- ቀኑ በውል ተለይቶ ባልታወቀ ህዳር ወር 2008 ዓ.ም ለ15ኛ ምስክር ስልክ በመደወል በሁሉም የኦሮሚያ ከተሞች ህገ ወጥ ሰልፍ እና ተቃውሞ እየተደረገ ነው በሚል በጉጂ ዞን የተለያዩ ወረዳዎች ይህን ተግባር እንዲያስተባብር እና ሪፖርት እንዲያደርግለት ተቃውሞውንም ሲያከናውኑ መንገድ በመዝጋት፣ በመንግስት የፀጥታ አካላት ላይ ረብሻ እና ብጥብጥ በማንሳት፣ የታሰሩ ሰዎች እንዲፈቱ በማድረግ መሆን እንዳለበት ተልዕኮ በመስጠት በሰባቦሩ ወረዳ በሰባቦሩ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና በሸኪሶ ወረዳ በሸኪሶ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና በጉጂ ዞን የተከሰተውን እንዲሁም በመደወላቡ የነበረው የሽብር ተግባር ሲመራ የነበረ በመሆኑ፣ይህንኑ ተግባር በቀን 10/3/08 ዓ.ም የአርበኞች ግንቦት ሰባት እየተባለ ለሚጠራው የሽብር ቡድን ልሳን ለሆነው ኢሳት ሬድዮ እና ቴሌቪዥን ፕሮግራም አዘጋጅ ካሳሁን ይልማ እና ለሽብር ቡድኑ አመራር ጃዋር ሙሀመድ ሪፖርት ሲደርግ የነበረ በመሆኑ፣

4ኛ.ተከሣሽ በቀለ ገርባ

- ቀኑ ባልታወቀ ከነሀሴ2007 ዓ/ም ከእስር ከተፈታ በኋላ የኦፌኮ ሥራ አስፈፃሚነቱን ሽፋን በማድረግ በውጪ ሀገር ከሚገኙ የኦ.ነ.ግ. አመራሮች ጋር በአሜሪካን አገር በመገናኘት ወደ ሀገር ውስጥ ሲመለስ የሽብርና የአመፅ ተልእኮ በመቀበል ኦሮሚያ ላይ መቀጣጠል እንዳለበት ተልእኮ በመስጠት የሥራ ክፍፍል በማድረግ [illegible] ኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን አዳማ ከተማ ከ2ኛ ተከሣሽ [illegible] ሸዋ ዞን አምቦ ከተማ ከ1ኛ ተከሣሽ



unverified

http://ethcriminalawnetwork.com



ጉርሜሳ እያና በኦሮሚያ ክልል ፊንፊኔ ዙሪያ ቡራዩ ከተማ በመመደብ 3ኛ ተከሣሽ አዲሱ በላላ ጉጀለን ቡሌ ሆራ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ አመፅ እንዲነሳ/እንዲደረግ/ አመራር ሰጥቷል በ2008 ዓ/ም በኦሮሚያ ዞን በሚገኙ ወረዳዎችና ቀበሌዎች የኦፌኮ አባሎች ደርጀቱን እንደሽፋን በመጠቀም የኦ.ነ.ግን የሽብር ተልእኮ ለማሳካት ለአመፅ እንዲደራጁ በማድረግ በአካባቢው ያሉትን የመንግስት መዋቅሮች እንዲፈርስ እንዲቃጠል መንገዶች እንዲዘጉ በፀጥታ ኃይሎች እና ሰላማዊ ሰዎች ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማስደረግ፡፡ በምእራብ ሸዋ ዞን አምቦ፣ ግንደበረት ጊንጪ በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን በተለያዩ ወረዳዎች ዩኒቨርስቲዎች ፣ትምህርትቤቶች ፣ ቄለም ወለጋ ዞን፣ ደቡብ እምራብ ሸዋ ዞን አመያ ወረዳ ፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ቡራዩ፣ ሱልልታ በጉጂ ዞን የተለያዩ ወረዳዎችና ዩኒቨርስቲዎች እና በምስራቅ ሸዋ አካባቢ የአመፅ እንቅስቃሴ በማስደረግ የሰው ሕይወት እንዲጠፋ የአርሶ አደሮች የከተማ ነዋሪዎች ንብረት እንዲወድም በእሳት እንዲጋይ የመንግስት ተቋማት እንዲቃጠሉና እንዲወድም የፀጥታ ኃይሎች አባላትን እንዲገድሉ የኢንቨስተሮች ንብረት እንዲወድምና እንዲቃጠል አመፅ እንዲቀጣጠል አመራር በመስጠት በማስተባበር ተሳታፊ ሆናል፡፡

5ኛ <u>አብደታ ነጋሳ</u>

- ቀኑ እና ወሩ ባልታወቀ 2008 ዓ.ም ጀምሮ በሽብር ቡድኑ በህቡዕ የተደራጀ ሲሆን ለሽብር ቡድኑ አባላት ከሆኑ የአቃቂ ሳይንስና ቴክኖሎጂ እና ከስድስት ኪሎ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ጋር በመሆን የቅስቀሳ ስራዎችን ሲሰራ እና የቅስቀሳ ወረቀቶችን በማሳተም ሲንቀሳቀስ የነበረ ሲሆን በቀን 08/04/08 ዓ.ም እና በቀን 10/4/08 ዓ.ም ታሬ ለተባለው የመቀሌ ዩንቨርስቲ እና የኦነግ ተጠርጣሪ ለሆነው ግለሰብ ጋር በመገናኘት ዝግጅታቸውን ከጨረሱ በኂላ በኦሮሚያ ክልልና ከዚ ውጪ በሚገኙት ዩኒቨርስቲዎች አመፅ ተግባሩ በአንድ ጊዜ የሚነሳበት ሁኔታ ላይ የሴል አባላት እንዲነጋገሩ እና የአመፁ አስተባባሪዎች ቀድመው ከግቢ እንዲወጡ፣ እስከዚያ ግን በጥንቃቄ የማደራጀት



unverified

http://ethcriminalawnetwork.com

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በፍትህ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር........................
Re.NO
ቀን................................
Date

አባላቱ እንዲመካከሩ እና ለውይይት ህዝቡ ቢጣራ መሄድ እንደሌለባቸው እና እስከ ትጥቃቸው ጫካ መግባት እንዳለባቸው ተልዕኮ የሰጠ በመሆኑ፣

7ኛ. ተከሣሽ ጭምሳ አብዲሳ

- በጅማ ዩኒቨርስቲ በመማር ላይ እያለ ቀንና ወሩ ባልታወቀበት ለኦ.ነ.ግ የሽብር ቡድን በአባልነት ተመልምሎ በዩኒቨርስቲው ውስጥ አባላትን በማደራጀት፣ በማንቀሳቀስና በማስተባበር በ2007 ዓ/ም ጀምሮ በሕቡዕ በመንቀሳቀስ በተሰጠው ተልእኮ በኦፍኮ ፖርቲ ሽፋን በተከሣሹ ደጀኔ ጣፋ በማድረግ በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ በሚዳቀኚ ኤጀራ ወረዳ ቡራዩ እና ሆለታ አካባቢ በመዘዋወር የሽብር አመፁ እንዲካሄድ ሲንቀሳቀስ የነበረ፣ በመስከረም ወር 2008 ዓ/ም በተከበረው የኤሬቻ በዓል ለኦ.ነ.ግ የሽብር አባላትን በማደራጀትና በመመልመል ሕዳር 2008 ዓ/ም ግርማ ነጋሳ ከተባለው የሽብር ቡድኑ አባል ጋር በስልክ በመገናኘት በኦሮሚያ ክልል ማስተር ኘላንን በተመለከተ በምእራብ ሸዋ ሚዳቀኚ ወረዳ ተማሪዎች ለአመፅ እንዲወጡ አመፁን እንደሚመራ ሪፖርት በማድረግ እንዲሁም የተሰጠውን የሽብር ተልእኮ ለማስፈፀም እንዲችል መደላወቡ፣ በአምቦ፣ አዳማ፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ከሚገኙት ለሚኘው የኦ.ነ.ግ የሴል አባላትን አነጋግሮ እንደተመለሰ በ8/2/2008 ዓ/ም ደረጀ ለተባለ ቡራዩ አካባቢ ለሚኖር የኦ.ነ.ግ አባል ገልያለታል በሕቡዕ ከማንቀሳቀሱ አባላት ጋር በመሆን አመጽና ሁከት እንዲስፋፋ መንገዱ እንዲዘጋ በፀጥታ ኃይሎች ላይ በድንጋይና በተለያዩ ቁሳቁሶች በማስወርወር አደጋ እንዲደርስ የሽብር ተልእኮውን በማስፈፀም ተሣታፊ ሆኗል፡፡

8ኛ.ተከሣሽ ጌቱ ግርማ

- በኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት የኦዲት ባለሙያ ሆኖ የኦነግን ተልኮ ለማሳካት በኦ.ነ.ግ. የሴል አባል በመሆን በመደራጀት በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን የሱልልታ አካባቢ አስተባባሪ በመሆን በሰሜን ሸዋ ኩዩ ገብረጉራቻ አካባቢ የኦ.ነ.ግ. ሴል መደራጀቱን [illegible] ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ

ቴሌ ፋክስ 755061 ስልክ 764014 የፖ.ሣ.ቁ. 1370 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Fex ---------------- Tel. 51 50 99 P.O. Box 1370 Addis Ababa Ethiopia
"ፍትህ በተለወጠ አመራር ፣ በተለወጠ ሠራተኛ ፣ በተለወጠ ተቋም፣"



unverified

http://ethcriminalawnetwork.com

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በፍትህ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር........................
Re.NO
ቀን..................................
Date

መፍጠር እንዳለበት በ6/03/2008 ዓ/ም ውጪ ለሚገኝ ለቡድኑ አባል መረጃ አስተላልፏል በ3/4/2008 ዓ/ም ተከሣሽ ፍራኦል ቶላ ጋር የስልክ ግንኙነት በማድረግ ከሚታ ሮቢ የሴል አባላት ሁለት የጦር መሣሪያ ስለሰጣቸው ለአመጽ ተግባር እንዳሆን ካሳሁን ከተባለ የቡድኑ አባል እንዲወስድ መልእክት አስተላልፏል፡፡

- በሰሜን ሸዋ ወረጃርሶ አካባቢ ለሚደረገው አመፅ መንገድ እንዲዘጋ ለአመጽ ሁለት ቦንብ መግዣ ገንዘብ እንደሚሰጥ ለተቃውሞ ሰልፍ ሕፃናትን ከፊት በማድረግ አዋቂዎች ከኃላ እንዲሆኑ መንገዱን እንዲዘጉ በ3/4/2008 ዓ/ም ለአንድ የቡድኑ አባል በስልክ መልእክት አስተላልፎአል የአመፁን እንቅስቃሴ ለመደገፍ ከምእራብ ሸዋ ዞን ግንደበረት የኦ.ነ.ግ ታጠቂ ቡድን ወደ ሰሜን ሸዋ እንደሚንቀሳቀስ ተከሣሽ በ6/4/2008 መልከት አስተላልፏል ፊንፊኔ ዙሪያ ሱልልታ ከተማ አመፅ በመጀመር ያለቀው ሕዝብ ይለቅ በማለት በ2008 ዓ/ም በታህሣስ ወር ሱልታ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የሽብር ቡድኑ ባነሰው አመፅ የሱልልታ ማዘጋጃ ቤት እንዲቀጥል በማስተባበር ተሣታፊ ሆኗል፡፡

<u>9ኛ.ተከሣሽ ፍራኦል ቶላ</u>

- ቀንና ወሩ ባልታቀበት ከ2007 ዓ/ም በውጭ ከሚገኙ የኦ.ነ.ግ የሽብር ቡድን አመራሮች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ለሽብርና ለአመፅ ቡድኑ በጅማ አካባቢ ያለው አደረጃጀት በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን እንዲቀጥል ለተከሣሽ ጌቱ ግርማ መልእክት በማስተላለፋ የሽብር ቡድኑ አባላት ወታደራዊ ስልጠና እንዲያገኙ መልምለው ወደ ኬንያ እንዲልኩ መልእክት በማስተላለፍ፤
- በ2008 ዓ/ም በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የተቀናጀ የጋራ ማስተር ኘላን እና የኦሮሚያ ከተሞች እድገት ኘላን አዋጅ በተሳሳተ መንገድ በመተርጐም በኦሮሚያ ክልል የተቀሰቀሰው የሽብር አመፅ ለኦ.ነ.ግ ምቹ አጋጣሚ በመሆኑ አመፁ እንዲቀጣጠል ከተከሣሽ ጌቱ ግርማ ጋር ግንኙነት በመፍጠር በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ገብረጉራቻ ሱሉልታ ቡራዩ ከተማ የሽብር አመፅ እንዲንቀሳቀስ በማስተባበር በተፈጠረው አመፅ በሰሜን ሸዋ ዞን



unverified

http://ethcriminalawnetwork.com



የመማር ማስተማር ሂደት እንዲቋረጥ በሱልልታ የከተማው ማዘጋጃ ቤት እንዲቀጠል እንዲሁም የቡራዩ ከተማ የሕዝብ ማመላለሻ አንበሳ የከተማ አውቶብስ እንዲቃጠል በማስተባበር ተሳታፊ ሆኗል፡፡

10ኛ. ተከሣሽ ጌታቸው ደረጀ ቱጁባ

- በኦፍኮ ፖርቲ ሽፋን በኦ.ነ.ግ የሽብር ቡድን አባልነት በመደራጀት በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ዞን በሚገኙ ወረዳዎች ሕዝባዊ አመፅ እየተጠናከረ ስለሆነ ወደ ትውልድ ቦታቸው በመሄድ አመራር መስጠት እንደሚገባቸው ለኦ.ነ.ግ የሴል ቡድኑ አባላት ለተከሣሽ ለደጀኔ አብዲሳ ወይም ጭምሶ አብዲሳ በኦ.ነ.ግ ሴል አስተባባሪ በ2/4/2008 ዓ/ም መልእክት አስተላልፎአል በመላው ኦሮሚያ የአመፅ እንቅስቃሴው እየተጠናከረ ስለሆነ ይበልጥ እንዲቀጣጠል ለሚያውቋት የሴል አባላት ስልክ በመደወል እንዲበረታቱ መቀስቀስ እንደሚገባቸው በ4/4/2008 ዓ/ም ገላና ለተባለው የኦ.ነ.ግ የሴል ከአዲስ አበባ አባል ገልፆለታል፡፡ በሚኖርበት ወረዳ እየተደረገ ያለው የአመፅ እንቅስቃሴ በፀጥታ አስከባሪዎች ላይ የጦር መሣሪያ መቀማት፣ ፖሊስ ጽ/ቤት ማቃጠል እራሳቸውን ለመከላከል እና ውጊያ ለመግጠም በዝግጅት ላይ እንደሚገኙ በሜታ ሮብ አዳአ በርጋ የሚገኙ ወጣቶች ከፀጥታ አካላት ጋር ውጊያ ለመግጠም እንደተዘጋጁ ከኦነግ ታጣቂ ቡድን ጋር በመቀላቀል ለመታገል ሃሣብ እንዳላቸው በ2/4/2008 ዓ/ም ለአንድ የሽብር ቡድኑ አባል ከአዲስ አበበባ ገልፆለታል፡፡
- በምዕራብ ሸዋ ዞን ኤጀሬ ወረዳ ውስጥ የኦ.ነ.ግ. ታጣቂ አባላት እርምጃ መውሰድ እንዲጀምሩ በሌሎች ኦሮሚያ አካባቢዎች የእርምጃ አወሳሰዱና አመፅ እንቅስቃሴው ወደ ተሻለ ደረጃ እያደገ መሆኑን በ15/4/2008 ዓ/ም ለአንድ የቡድኑ አባል መልእክት አስተላልፎአል፡፡ የመጀመሪያው አመፅ እየተዳከመ በመምጣቱ በሁለኛው ዙር አመፅን በአዲስ መልክ ለማቀጣጠል ዝግጅት መደረጉን በ16/4/2008 ዓ/ም በላይ ዋቅሳ በተባለ የኦ.ነ.ግ. አባል ከአዲስ አበባ በስልክ መልእክት በማስተላለፍ የኦ.ነ.ግን የሽብር አመፅ ለማሳካት ተሳታፊ ሆኗል፡፡



unverified

http://ethcriminalawnetwork.com



11.ተከሣሽ በየነ ሩዳ

- ከ3/11/2007 ዓ/ም ጀምሮ በሚኖርበት ምእራብ ሸዋ ዞን የኦ.ነ.ግን የሽብር ተልእኮ ለማስፈፀም አምቦ ከተማ በመሆን በጅማና ኢሊባቡር አካባቢ የሚደረገው የኦ.ነ.ግ ሴል አባላትን ለአመፅ የማዘጋጀት ሥራ እየተሰራ ስለሆነ በቋሚነት ኘሮግራም ተይዞ ከየአካባቢው የኦ.ነ.ግ ሴል አስተባባሪዎች ጋር እየተገናኙ መሄድ እንደሚገባቸው የኦ.ነ.ግ ተልእኮ ለማሳካት የትጥቅ ትግል አመፅ በማስነሳት እንቅስቃሴ ወደ ሕዝባዊ አመፅ የመቀየር ሥራ እንደሚገባ ለተከሳሽ ተስፋዬ ሊባን ከወሊሶ መልእክት በማስተላለፍ ሕዝቡን ለአመፅ እንዲዘጋጅ የጦር መሣሪያ ከመንግስት ማከማቻ እንዲወስዱ እና እንዲካፈሉ ተከሣሽ በ30/02/2008 ዓ/ም ለተከሣሽ አሸብር ደሳለኝ ጋር መረጃ ልውውጥ በማድረግ የተጀመረው አመፅ እንዲፈነዳ ተጠናክሮ እንዲቀጥል በ27/2/2008 ዓ/ም ለተከሣሽ ተስፋዬ ለባን መልእክት አስተላልፋአል፡፡ ባህላዊ የጦር መሣሪያና በእቃ የተሞሉ ጋዝ አዘጋጅተው መጠቀም እንዳለባቸው በ16/03/2008 ዓ/ም ከወሊሶ ለተስፋዬ ለባን መመሪያ አስተላልፏአል፡፡
- የኦ.ነ.ግ ሴል አደረጃጀት ተጠናክሮ መቀጠል እንደሚያስፈልግና በሥራው ላይ በርትተው መንቀሳቀስ አስፈላጊ በመሆኑና በ19/03/2008 ዓ/ም ለባንዱ ዳንኤል የኦ.ነ.ግ ሴል አስተባባሪ ከነቀምቴ መልእክት በማስተላለፍ የመንግስት ተቋማትን በሂደት በመቆጣጠር አመፅን ማጠናከር እንደሚገባ አመፅ የሚጠራው ሀገር ውስጥ ባለው በኦ.ነ.ግ ሴል እንደሆነ የሚቀጥል መሆኑን በማህበራዊ ድረ ገጽ ላይ ፖስት መደረግ እንዳለበት የኦ.ነ.ግን የሴል መዋቅርን ማጠናከር እንደሚገባ በ2/4/2008 ዓ/ም ለተከሣሽ አሸብር ደሳለኝ መመሪያ ሰጥቷል እንዲሁም የአመፅ እንቅስቃሴው መጠናከር እንዳለበት በአመፅ ወቅት የመንግስት ንብረት ወደ ራሣቸው በማምጣት መጠቀም እንደሚኖርባቸው ከአቅም በላይ የሆነውን ማቃጠል እንደሚገባ በ4/4/2008 ዓ/ም መልእክት በማስተላለፍ እንዲሁም በአመፁ ወቅት በመስተዳድር በካቢኔ አባላት እና



unverified

http://ethcriminalawnetwork.com

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በፍትህ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር........................
Re.NO
ቀን.................................
Date

13ኛተከሣሽ አሸብር ደሳለኝ

- የኦ.ነ.ግ የሽብር ቡድን አባልና ከሆኑት ተከሣሽ በየነ ሩዳ ና ተከሣሽ ተስፋዬ ሊበን ጋር በመሆን የኦ.ነ.ግን. የሽብር ተልእኮ ለማሳካት ከውጭ ሀገር የሚኖሩ የሽብር ቡድኑ አመራሮች ተልእኮ በመቀበል በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ከተማ ለኦ.ነ.ግ አባልነት በሴል ሲያደራጅ የነበረ በኦሮሚያ ምእራብ ሸዋ ዞን የተነሳው አመፅ በኦ.ነ.ግ ሴል አባላት እየተመራ መሆኑን እንደማያውቁ በመጠቆም የሴል መዋቅርን ማጠናከር እንደሚገባ አስገዳጅ ሁኔታዎችን ለመፍጠር መንቀሳቀስ አስፈላጊ መሆኑን በቁልፍ ተቋማት ላይ እርምጃ መውሰድ እንዳለበት በ07/4/2008 ዓ/ም ቢሾፍቱ ለሚገኙ የቡድን አባላት መረጃ አስተላልፏል በአምቦ እና በጊንጮ በጀርሶ የተቀሰቀሰው የሽብር አመፅ ወደ አምቦ ከተማ እንዲቀጥል ተማሪዎች ትምህርት እንዲያቆሙ ከመንግስት ግምጃ ቤት 108 ጦር መሣሪያ እንደተዘረፈ በኤርትራና ከኬንያ ስልጠና የወሰደ 30 የኦ.ነ.ግ የሽብር ቡድን ታጣቂዎች ወደ ሀገር ውስጥ የገባ መሆኑን ተከሣሽ በየነ ሩዳ ሪፖርት ሲያደርግ የነበረ በምእራብ ሸዋ እና በደቡብ ምእራብ ሸዋ ዞን አመያ ወረዳ የበርካታ አርሶ አደሮች ቤትና ንብረት እንዲቃጠል በአካባቢው ባሉ ከኦሮሞ ብሔር ውጭ በሆኑ ብሔረሰቦች አካባቢውን ለቀው እንዲወጡ በማድረግ በንብረታቸው ላይ ጥቃት ማድረስ በፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን በቡራዩ ከተማ የህዝብ ማመላለሻ አወቶብስ እንዲቃጠል የሱሉልታ ማዘጋጃ ቤት እንዲቃጠል በተፈፀመው የሽብር ድርጊት በዋናነት በማስተባበር ተሳታፊ ሆኗል፡፡

2ኛ ክስ

ከ14ኛ ተከሳሽ እስከ 22ኛ ተከሣሽ

ወንጀሉ

በ1996 ዓ/ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7\13 በመተላለፍ ወንጀል መፈፀም፡፡



unverified

http://ethcriminalawnetwork.com



ሚሊሻ ላይ እየተለዩ ርምጃ እንዲወሰድባቸው ማድረግ የሌላ ብሔረሰብ ተወላጆችንም በመለየት እርምጃ ሊወሰድባቸው እንደሚገባ ተከሣሽ በ13/4/2008 ዓ/ም ወለጋ ላለ አንድ የቡድኑ አባል መልእክት በማስተላለፍ በጥቁር አንጭኒ አካባቢ ያለው የአመፅ ሁኔታ ቀጣይነት እንዲኖረው አመፁን አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባቸው በ13/4/2008 ዓ/ም ፌዬራ ለተባለ የኦ.ነ.ግ. ተጠርጣሪ በመግለጽ ተከሣሽ በኦሮሚያ ክልል ምእራብ ሸዋ እና በደቡብ እዕራብ ሸዋ ከሚገኙ የኦ.ነ.ግ. የሽብር ቡድን የሴል አባላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር አመፅ እንዲቀጣጠል በማድረግ ተሣታፊ ሆኗል፡፡

12ተከሣሽ ተስፋዬ ሊበን

- በሚኖርበት ኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ወሊሶ ወረዳ ከ2007 ዓ/ም ጀምሮ በኦ.ነ.ግ. የሽብር ቡድን በዕቡዕ በሴል በመደራጀት ከተከሣሽ በየነ ሮዳ እና በውጪ ሀገር ከሚገኙ የኦ.ነ.ግ አመራሮች ጋር ግንኙነት በመፍጠር በ2008 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምእራብ ሸዋ ዞን ጊንጪ የተቀሰቀሰውን የሽብር አመፅ ወደ ደቡብ ምእራብ ሸዋ እንዲመጣ በማድረግ በሕቡዕ በማደራጀት በወሊሶ እና በአመያ የከተሞች የሽብር አመፅ እንዲንቀሳቀስ የበርካታ አርሶ አደሮች ቤተሰብ ቤትና ንብረት እንዲቃጠል በኦሮሞ ቤተሰብ ውጪ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በአካባቢው ለቀው እንዲሄዱ የፀጥታ ሀይል የሽብር አመፅን እንዳይከላከል መንገዶች እንዲዘጉ በማድረግ የመንግስት መዋቀሮች እንዲፈርስ እንዲወድሙ በማድረግ በማስተባበር የተሳተፈ በመሆኑ፤
- በ3/12/2007 ዓ/ም ከተከሣሽ በየነ ሮዳ በስልክ ግንኙነት በማድረግ አመፅ በ3 መንገድ መቀጣጠል እንዳለበት 1 አመፅ 2 በትጥቅ ትግል 3. በሕዝባዊ አመፅ በተቀናጀ የኦ.ነ.ግ ሴል አባላት አመፀ እንዲነሳ ቅድመ ሁኔታ መደረግ ያለበት መሆኑን በ16/3/2008 ዓ/ም ከተከሣሽ በየነ ጋር የስልክ ግንኙነት በማድረግ በኦሮሚያ ደቡብ ምእራብ ሸዋ ዞን የተደረገውን አመፅ በመምራት ተሳታፊ ሆኗል፡፡



unverified

http://ethcriminalawnetwork.com



ከውጭ ሀገር ሁኖ 8,068.64 (ስምንት ሺ.ህ ስልሳ አራት ብር ከስልሳ አራት ሳንቲም) ወይም 400 (አራት መቶ ዶላር) በአንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ ለገሀር ቅርንጫፍ በተስፋዬ ደገፋ ስም የላከለትና ገንዘቡን የተቀበለ በመሆኑ፤

- ተከሣሹ ለሽብር ድርጅቱ አባላትን እንዲመለምል በተሰጠው ተልእኮ መሰረት ቀኑ ባልታወቀ ነሀሴ ወር 2007 ዓ/ም ዲናኦል የአባቱ ስም ያልታወቀና ተሻለ ተሬሣን ፣ ቀኑ ባልታወቀ መስከረም ወር 2008 ዓ/ም ሁንዴ የአባቱ ስም ያልታወቀና ሀቡሱ አስፋውን እና ህዳር 4 ቀን 2008 ዓ/ም የሱፍ አለማሁንና ሂካ ተክሉን ለኦ.ነ.ግ. የሽብር ድርጅት አባል እንዲሁኑ ውጭ ሀገር ከሚገኘው የሽብር ድርጅቱ አመራር ከሆነው ጌታቸው ጉተማ ጋር በማገናኘት ለኦነግ አባልነት ተመልምለው ዳናኦል ፣ ተሻለ ተሬሣ፣ ሁንዴና ሀቡሱ የሽብር ድርጅቱ ወደ ሚገኝበት ኬንያ እንድሄድ ያደረገ በመሆኑና የሱፍ አለማየሁና ሂካ ተክሉንም ወደ ኬንያ በመሄድ ከሽብር ድርጅቱ ጋር ተቀላቅለው ወታደራዊ ስልጠና እንዲወስድ ለማድረግ ወደ ኬኒያ እንዲሄዱ በመንገር ወደ ኬንያ ለመሄድ በጉዞ ላይ እያሉ ህዳር 6 ቀን 2008 ዓ/ም ሞያሌ ከተማ ላይ በፀጥታ ሀይሎች የተያዙ በመሆኑ ተከሣሹ ከላይ የተዘረዘሩትን ግለሰቦች ለሽብር ድርጅቱ በአባልነት የመለመለ በመሆኑ፤
- ተከሣሹ ከላይ በተገለፀው አግባብ ለሽብር ድርጅቱ በሀገር ውስጥ ያሉ ሁኔታዎችን መረጃ እንዲሰጥ በተሰጠው ተልዕኮ መሰረት ለሽብር ድርጅቱ አመራሮች ጌታቸው ጉተማ እና ሌሎች ለጊዜው ስማቸው ካልታወቁ የሽብር ድርጅቱ አባላቶች በፌስ ቡክ አድራሻቸውና በስልክ ቀኑና ወሩ ባልታወቀ ከ2006 ዓ/ም ጀምሮ በሀገሪቱ እየተካሄደ ያለው ምርጫ ሣይሆን ጦርነት ነው ፣ የመንግስት አካላት ምርጫው ሣይጀመር ኮሮጆውን በወረቀት ሞልተውታል ፣ ታዛቢዎች ከምርጫ ጣቢያው እየተባረሩ ነው፣ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ እና በዩንቨርስቲ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የወጣቶች አደረጃጀት ስላለ በሰላማዊ ትግል ለውጥ ማምጣት ስለማይቻል ከኦ.ነ.ግ. ጋር አብረው በድብቅ እንዲሰሩ በማድረግ በሀገሪቱ ላይ በአንድ ቀን በተመሣሣይ ሰዓት የተቃውሞ ሰልፎችን ማድረግ ይቻላል፣ የአዲስ አበባና ፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ማስተር ኘላን ተግባራዊ እንዳይሆን ወጣቶች በተደራጀ መልኩ የተቃውመ ሰልፎችን ማካሄድ



unverified

http://ethcriminalawnetwork.com



አለባቸው የሚሉና መሰል ጉዳዮችን ለሽብር ድርጅቱ አመራሮች በፌስቡክ እና በስልክ መረጃ ሲሰጥ የነበረ በመሆኑ፤

15ኛ ተከሳሽ የሱፍ አለማየሁ

- ተከሣሽ ቀኑ ባልታወቀ ጥቅምት ወር 2008 ዓ/ም ለኦነግ የሽብር ድርጅት አባል በመሆን የሽብር ድርጅቱን አላማና ተልዕኮ ለመፈፀም እንዲቻል ወደ ኬኒያ በመሄድ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ስልጠና ለመውሰድ በማሰብ ህዳር 5 ቀን 2008 ዓ/ም ከአዲስ አበባ በመነሳት በሞያሌ አድርጎ ወደ ኬኒያ ለመሄድ የሽብር ድርጅ አባል ከሆነው ሂካ ተክሉ ጋር በጉዞ ላይ እያሉ ህዳር 6ቀን 2008 ዓ/ም በሞያሌ ከተማ በፀጥታ ሀይሎች የተያዘ በመሆኑ፤

16ኛ ተከሳሽ ሂካ ተክሉ

- ተከሣሽ ቀኑ ባልታወቀ ጥቅምት ወር 2008 ዓ/ም ለኦነግ የሽብር ድርጅት አባል በመሆን የሽብር ድርጅቱን አላማና ተልዕኮ ለመፈፀም እንዲቻል ወደ ኬኒያ በመሄድ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ስልጠና ለመውሰድ በማሰብ ህዳር 5 ቀን 2008 ዓ/ም ከአዲስ አበባ በመነሳት በሞያሌ አድርጎ ወደ ኬኒያ ለመሄድ የሽብር ድርጅ አባል ከሆነው የሱፍ አለማየሁ ጋር በጉዞ ላይ እያሉ ህዳር 6ቀን 2008 ዓ/ም በሞያሌ ከተማ በፀጥታ ሀይሎች የተያዘ በመሆኑ፤

17ኛተከሳሽ. ገመቹ ሻንቆ

ተከሣሽ ቀኑና ወሩ ባልታወቀ በ2008 ዓ/ም ለኦ.ነ.ግ. የሽብር ድርጅት አባል በመሆን በሀገር ውስጥ ለሽብር ድርጅቱ አባላቶችን በመመልመልና ወደ ኬንያ ሀገር በመላክ ወታደራዊ ስልጠና እንዲያገኙ ከሚያመቻቸው ደረጀ መርጋ ጋር በስልክ በመገናኘት ወደ ኬንያ በመሄድ ከሽብር ድርጅቱ ጋር በመቀላቀል ወታደራዊ ስልጠና በመውሰድ በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት በሀይል ከስልጣን ማውረድ ስላለብን የሽብር ድርጅቱ ወደሚገኝበት ቦታ እንድሄድ አመቻችልኝ በሚል ጥያቄ አቅርቦለት ደረጀ መርጋ በበኩሉ ሀገር ውስጥ በመሆን ወጣቶችን ለኦ.ነ.ግ መመልመልና መላክ ስላለብን አንተም ሀገር ውስጥ ሁነህ አባላቶችን መመልመልና መላክ አለብህ በሚል ተልእኮ ሰጥቶት ተልእኮውን በመቀበል ቀኑ በውል ተለይቶ ባልታወቀ ህዳር ወር 2008 ዓ/ም የሽብር



unverified

http://ethcriminalawnetwork.com



ድርጅቱ አባል የሆነው ደረጀ መርጋ ጋር በስልክ በመገናኘት የሽብር ድርጅቱን ለመቀላቀል የሚሄዱትን ሁለት አባሎች የሱፍ አለማየሁንና ሂካ ተክሉን ስልክ እየደወልክ አበረታታቸው ብሎደረጀ መርጋ ተልዕኮ ሰጥቶት ተከሣሹ ለየሱፍ አለማየሁ ስልክ በመደወል በቀርብ ጊዜ ወደ ኬኒያ እንድትሄድ እየተመቻቸ ነው በማለት የነገራቸው እና ህዳር 05 ቀን 2008 ዓ/ም የሱፍ አለማየሁ እና ሂካ ከሽብር ድርጅቱ ጋር ለመቀላቀል ወደ ኬኒያ በጉዞ ላይ እያሉ ለየሱፍ አለማየሁ ስልክ በመደወል ሞያሌ ላይ የሚቀበላችሁ ሰው ስለተዘጋጀ አትፍሩ በማለት ከሽብር ድርጅቱ የተሰጠውን ተልእኮ ሲፈፅም የነበረ በመሆኑ፤

18ኛተከሳሽ መገርሳ አስፋው

ተከሳሹ እራሱን የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦ.ነ.ግ) ብሎ በሚጠራው የሽብር ድርጅት ውስጥ ቀኑ ባልታወቀ ጥቅምት ወር 2008 ዓ.ም ጀምሮ የአዲስ አበባ እና የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን የተቀናጀ ማስተር ፕላን የኦሮሞን ህዝብ የሚጎዳ በመሆኑ ከኦነግ የሽብር ድርጅት ጋር በመቀላቀል በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት በትጥቅ ትግል መታገል አለብኝ በሚል የሽብር ድርጅቱ አባል በመሆን ወደ ኬኒያ በመሄድ ከሽብር ድርጅቱ ጋር በመቀላቀል ወታደራዊና ፖለቲካዊ ስልጠና ለመውሰድ በማሰብ ታህሳስ 12 ቀን 2008 ዓ.ም ከአዲስ አበባ በመነሳት ሒርጳ ፣ ታሪኩ ፣ ጋሹ ከተባሉ ለጊዜው የአባታቸው ስም ያልታወቁ እና ጉልቻ አንጌ ከተባሉ የሽብር ድርጅቱ አመራሮችና አባሎች ጋር ስልክ በመደዋወል ሞያሌ ድረስ እንዲመጣና ኬኒያ ድንበር አካባቢ የሚቀበቀው አባል እንደሚያመቻቹለት ነግረውት ቡሌ ሆራ ከተማ በመሄድ ለተወሰነ ጊዜ እዛው ከቆየ ብኃላ ታህሳስ 24 ቀን 2008 ዓ.ም ከቡሌ ሆራ ከተማ በመነሳት ወደ ሞያሌ በመሄድ ከሽብር ድርጅቱ የተላከውንና ወደ ኬኒያ የሚወስደውን ሰው በመጠበቅ ላይ እያለ በፀጥታ ሀይሎች የተያዘ በመሆኑ

19ኛ ተከሳሽ ለሚ ኤደቶ

- ቀኑ በውል ተለይቶ ባልታወቀ መስከረም ወር 2008 ዓ.ም በቢሾፍቱ ከተማ ልዩ ቦታው ወርቁ ቢቂላ ሆቴል ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ቦንሳ ወርቁ በተባለው የሽብር ቡድኑ አባል አማካይነት ለሽብር ቡድኑ ተመልምሎ በመስማማት አባል የሆነ ሲሆን ከሌሎች



unverified

http://ethcriminalawnetwork.com

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በፍትህ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር.........................
Re.NO
ቀን...................................
Date

7 የሽብር ቡድኑ አባላት ጋር በመገናኘት የኦነግ (የሽብር ቡድኑ) ጠንካራ ወታደር ለመሆን ቅድሚያ ዝግጅት ለማድረግ የቴክዋንዶ ስልጠና ለመውሰድ እና ወደ ኬንያ ሄዶ ከሽብር ቡድኑ ታጣቂዎች ጋር ለመቀላቀል ተስማምቶ ቀኑ በውል ባልታወቀ መስከረም ወር 2008 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ህዳር ወር 2008 ዓ.ም ድረስ በሽብር ቡድኑ አባል ቦንሳ ወርቁ አማካኝነት ቡራዩ ከተማ ልዩ ስሙ ባጣሮ ሜዳ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የቴክዋንዶ ስልጠና ወስዶአል፡፡

- ህዳር ወር መጨረሻ 2008 ዓ.ም ከአብዲ ታምራት ጋር በመሆን ከአዲስ አበባ እና አዲስ አበባ ዙሪያ የተቀናጀ ማስተር ፕላን እና የኦሮሚያ ከተሞች እድገት ፕላን አዋጅን በሽብር አመፅ ለማስቆም በቡራዩ ከተማ የሽብር አመጽ እንዲነሳ በራሪ ወረቀቶችን በማዘጋጀት እና በማሳተም ለመበተን ሲንቀሳቀስ የተያዘ በመሆኑ፣

## 20ኛ. ተከሳሽ አብዲ ታምራት

- ቀኑ እና ወሩ በውል ተለይቶ ባልታወቀ 2006 ዓ.ም ወደ ኬንያ በመሄድ እና የሽብር ቡድኑ የሚሰጠውን ስልጠና በመውሰድ በ2007 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ አባላትን የመመልመል እና የማደራጀት ተልዕኮ ተቀብሎ ተመልሷል፡፡
- ህዳር ወር መጨረሻ 2008 ዓ.ም ከለሚ ኤዴቶ ጋር በመሆን በቡራዩ ከተማ ውስጥ የአዲስ አበባ እና አዲስ አበባ ዙሪያ የተቀናጀ ማስተር ፕላን እና የኦሮሚያ ከተሞች እድገት ፕላን አዋጅን በሽብር አመፅ ለማስቆም ቀስቃሽ በራሪ ወረቀቶችን በማሳተም ተሳትፎ የነበረው ሲሆን ይህንኑ ተግባሩን እና አጠቃላይ የነበረውን እንቅስቃሴ በፌስ ቡክ አድራሻ ስማቸው ጀቤሳ ቶኩማ እና ኢዶሳ ቀጄላ ለተባሉት የሽብር ቡድኑ አባላት ሪፖርት ሲያደርግ የነበረ በመሆኑ፣

## 21ኛ.ተከሳሽ አብዲሳ ኩመሳ ገኤሳ

ቀኑ በውል ተለይቶ ባልታወቀ ግንቦት ወር 2006 ዓ.ም ሀና ማሪያም ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በሊና ነመራ በተባለው የሽብር ቡድኑ አባል አማካኝነት ለሽብር ቡድኑ አባልነት ተመልምሎ ጉዳዩን በሚስጥር ለመያዝ የተስማማ ሲሆን ቀኑ በውል ተለይቶ ባልታወቀ ግንቦት ወር 2006 ዓ.ም ቁጥራቸው 18 ከሆኑ ሌሎች የሽብር ቡድኑ

ቴሌ ፋክስ 755061 ስልክ 7514 የመ.ሣ.ቁ. 1370 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Fex ---------- Tel. 51 50 99 P.O. Box 1370 Addis Ababa Ethiopia




unverified

http://ethcriminalawnetwork.com

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በፍትህ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር.........................
Re.NO
ቀን.................................
Date

አባላት ጋር ሀና ማርያም ኳስ ሜዳ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በመሰብሰብ የአባልነት ፎርም በመሙላት እና የአባልነት መዋጮ በማዋጣት ተሳትፎአል፡፡

በቀን 09/04/08 ዓ.ም በአዲስ አበባና አዲስ አበባ ዙሪያ የተቀናጀ ማስተር ፕላን እና የኦሮሚያ ከተሞች የእድገት ፕላን ሽፋን በማድረግ በተቀሰቀሰው የሽብር አመፅ ላይ ለመካፈል እና ከታጣቂ ቡድኑ ጋር ለመቀስቀል ከአዲስ አበባ በመነሳት ወደ ጀልዱ ሲሄድ የተያዘ በመሆኑ፣

22ኛ ተከሳሽ ሀልኮና ቀንጮራ

በቀን 06/03/08 ዓ.ም ወደ ኦነግ ታጣቂዎች ለመቀላቀል የሚሄዱትን ከሂካ ተክሉና የሱፍ አለማየሁ የተባሉትን ከሞያሌ መነሀሪያ ተቀብሎ ወደ ኬንያ ቴሶ ለማሻገር በመስማማት እና በስልክ በማገናኘት ወደ ኦነግ ታጣቂዎች ሊወስዳቸው ሲል የተያዘ በመሆኑ፣

በአጠቃላይ ተከሣሾች የኦ.ነ.ግን የሽብር ተልእኮ ለማሳካት በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ ዞን እና ወረዳዎች ሁከትና አመፅ እንዲነሳ አመራር በመስጠት በአመፁ ተሣታፊ በመሆን የበርካታ የሰው ሕይወት እንዲጠፋ፣ በሰው አካል ላይ ቀላልና ከባድ የአካል ጉዳት እንዲደርስ፣ በመንግስትና በህዝብ ተቋማት፣ በመሰረተ ልማት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዲደርስ በማድረግ እና በማስደረግ በዋና ወንጀል አድራጊት ተካፋይ በመሆን በፈፀሙት የሽብርተኝነት ድርጊቶችን የመፈፀም ወንጀል ተከሰዋል፡፡

ብርሃኑ ወንድምአገኝ
ረ/ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ

ፍቃዱ ፀጋ
ም/ረ/ጠቅላይ ዐ/ሕግ ||

ቴሌ ፋክስ 755061 ስልክ 764014 የመ.ሣ.ቁ. 1370 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Fex ............ Tel. 51 50 99 P.O. Box 1370 Addis Ababa Ethiopia
"ፍትህ በተለወጠ አመራር ፣ በተለወጠ ሠራተኛ ፣ በተለወጠ ተቋም፣"

unverified

http://ethcriminalawnetwork.com

...ራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
...ፍትህ ሚኒስቴር
...Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር.......................
Re.NO
ቀን.......................
Date

## ተከሳሾች ለፖሊስ የሰጡት የተከሳሽነት ቃል

1. 18ኛ ተከሣሽ መገርሳ አስፋው በወ \ ሥ \ ሥ \ ህ \ ቁጥር 27 \2 \ መሰረት ለፖሊ
   የሠጠው የተከሳሽነት ቃል 9 ገፅ
2. 16ኛ ተከሣሽ ሂካ ተክሉ በወ \ ሥ \ ሥ \ ህ \ ቁጥር 27 \2 \ መሰረት ለፖሊ
   የሠጠው የተከሳሽነት ቃል 7 ገፅ
3. 14ኛ ተከሣሽ ደረጀ መርጋ በወ \ ሥ \ ሥ \ ህ \ ቁጥር 27 \2 \ መሰረት ለፖሊ
   የሠጠው የተከሳሽነት ቃል 16 ገፅ
4. 15ኛ ተከሣሽ የሱፍ አለማየሁ በወ \ ሥ \ ሥ \ ህ \ ቁጥር 27 \2 \ መሰረት ለፖሊስ
   የሠጠው የተከሳሽነት ቃል 9 ገፅ
5. 17ኛ ተከሣሽ ገመቹ ሻንቆ በወ \ ሥ \ ሥ \ ህ \ ቁጥር 27 \2 \ መሰረት ለፖሊስ
   የሠጠው የተከሳሽነት ቃል 7 ገፅ
6. 6ኛ ተከሣሽ ገላና ናገሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/27/2/ መሰረት የሰጠው የተከሣሽነት ቃል 08 ገጽ
7. 20ኛ ተከሣሽ አብዲ ታምራት በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/27/2/ መሰረት የሰጠው የተከሣሽነት ቃል 10 ገጽ
8. 21ኛ ተከሣሽ አብዲሣ ኩመሳ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/27/2/ መሰረት የሰጠው የተከሣሽነት ቃል 08 ገጽ
9. 19ኛ ተከሣሽ ለሚ ኤዳቾ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/27/2/ መሰረት የሰጠው የተከሣሽነት ቃል 12 ገጽ
10. 7ኛ ተከሣሽ ጭምሳ አብደሳ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/27/2/ መሰረት የሰጠው የተከሣሽነት ቃል 07 ገጽ
11. 12ኛ ተከሣሽ ተስፋዬ ሊበን በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/27/2/ መሰረት የተሰጠው የተከሣሽነት ቃል 06 ገጽ
12. 11ኛ ተከሣሽ በየነ ሩዳ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/27/2/ መሰረት የተሰጠው የተከሣሽነት ቃል 09 ገጽተከሣሽ ተስፋዬ ሊበን በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/27/2/ መሰረት የተሰጠው የተከሣሽነት ቃል 06 ገጽ
13. 8ኛ ተከሣሽ ጌቱ ግርማ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/27/2/ መሰረት የተሰጠው የተከሣሽነት ቃል 08 ገጽ

ቴሌ ፋክስ 755061 ስልክ 764014 የመ.ሣ.ቁ. 370 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Fex ------------ Tel ... 50 99 ... Box 370 ... Ethiopia

unverified

http://ethcriminalawnetwork.com

unverified